# የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት(ኢተፖድኅ) መሠረታዊ ሠነድ

# The Coalition of Ethiopian Opposition Political Organizations (CEOPO)

## መግቢያ

በኢትዮጵያ የሰላም የዲሞክራሲና የአንድነት ጥያቄ ፈር ይዞ የኢትዮጵያ ችግሮች በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት እንዲቻል እስከዛሬ እንቅፋት ሆነው ከቆዩት ምክንያቶች አንዱ በተቃዋሚዎች መካከል ሊኖር የሚገባው የትግል ህብረት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ያለማግኘት አንዱና ዋነኛው መሆኑን በማመን፤

በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ሊኖር የሚገባው የጠነከረ ኅብረትና የትግል አንድነት በሌለበት ሁኔታ ከቀጠለ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት በሚከተለው ኢዲሞክራሲያዊ ፖሊሲ አገራችን ለበለጠ አለመረጋጋትና ውድቀት የምታመራ መሆኑን በመገንዘብ፤

የሻዕቢያ አመራር እያካሄደ ባለው ወረራ፥ ከኢህአዴግ የተዛባ ፖሊሲ ጋር ተዳብሎ የበለጠ አገራዊ ጥፋት ሊያስከትል ይችላል የሚል እምነት ስለአሳደረብን፤

ይህንን በአገራችን ላይ እያንዣበበ ያለውን የጥፋት አደጋ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አንድ የጋራ የሆነ አማራጭ ይዘው በጋራ መታገልና ለትግሉ አመራር መስጠት የማይታለፍ ታሪካዊ ግዴታ መሆኑን በመቀበል፤ እኛ ስማችን በሰነዱ ማጠቃለያ ገጽ ላይ የተዘረዘረው ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.(September.11-13, 1998) በፓሪስ ከተማ የተሰበሰብነው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ለዚህ መሠረት የሚሆን የዓላማ አንድነትና የትግል ህብረት እንደህይወት እስትንፋስ የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ደርሰናል።
ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሣት በትከሻችን ላይ ወድቋል ብለን ከምናምነውና ከምንቀበለው ታሪካዊና ብሔራዊ አገር የማዳን ኃላፊነት በመነሣት ትግላችንን የምናስተባብርበትና ተደጋግፈን የጋራ ትግል ለማካሄድ የሚያስችለንን በድርጅታዊ እኩልነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት ከዚህ በታች በተመለከተው ሁኔታ መሥርተናል።

## ክፍል አንድ

### አንቀጽ 1 ሥያሜ

ኅብረቱ " <u>የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት</u> ወይም በአጭሩ "ኢተፖድኅ" በሚል ስም ይጠራል፤

---

አፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር፣ በኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ትንጅት፣ የኢትዮጵያ መድህን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ ኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት፣ ትግራይ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ትብብር፣ ትግራይ ትግሪኝ-ኢትዮጵያ--ኢትዮጵያውያን ቡድን ለሶሻል ዴሞክራሲ፣
AFAR REVOLUTIONARY DEMOCRATIC UNITY FRONT;— COUNCEL OF ALTERNATIVE FORCES FOR PEACE & DEMOCRACY IN ETHIOPIA;— COALITION OF ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES;— ETHIOPIAN MDHIN DEMOCRATIC PARTY;— OROMO NATIONAL CONGRESS;— SOUTHERN ETHIOPIAN PEOPLES DEMOCRATIC COALITION;— TIGRAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY;— TIGRAI-TIGRIGNI ETHIOPIANS FOR SOCIAL DEMOCRACY:

## አንቀጽ 2 የኢተፖድኅ ዓላማዎች

2.1. የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር
2.2. የኢትዮጵያ ብሄር/ብሔረሰቦች መብትና እኩልነት ተረጋግጦ ኢትዮጵያውያን በወንድማማችነት መንፈስ አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ ለማድረግ፤
2.3. በኢትዮጵያ ጦርነትም ሆነ የጦርነት አደጋ በማያዳግም ሁኔታ እንዲወገዱና ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን ለመታገል፤
2.4. በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፥የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ፍትሕ እንዲሰፍን፤
2.5. የሕግ የበላይነት እውን የሆነባት በዴሞክራሲ የምትዳደር ኢትዮጵያን ለመመሥረት በር ከፋችና ቅድመ ሁኔታ ለሆኑት ለዴሞክራሲ አመቺ የኃይል ሚዛን ለመፍጠርና ኢህአዴግን ለብሔራዊ ዕርቅ ለመጋበዝ፥ለነጻ ምርጫና ለዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት ለመታገል፤

## አንቀጽ 3 የኢተፖድኅ ተግባሮች

3.1. የኅብረቱን ዓላማዎች የተቀበሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች የተዋሃደ ድምፅ ሆኖ ማገልገል፤
3.2. የአጭር፥ መካከለኛና ረጅም የትግል ዕቅዶች በማውጣት በሕወሓት/ኢህአዴግ ላይ የሚካሄደውን የኅብረት ተቃውሞ ማስተባበር መምራት፤
3.3. ለህብረቱ ዓለማቀፋዊ የፖለቲካ፥የዲፕሎማሲ፥የገንዘብና ማንኛቸውንም ዓይነት ድጋፍ፥እርዳታና ትብብር መሻት፤
3.4. ስብሰባዎችን ሴሚናሮችን ማዘጋጀት፥ሰላማዊ ሰልፍ መጥራት ማስተባበር ሌሎች ተመሳሳይ እርምጃዎችን መውሰድ፤
3.5. በኅብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል የጠበቀ ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር መጣር፤
3.6. የተባበረ የሎቢና ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ለማድረግና ከመንግሥታትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች የሚገኘውን የትግል ድጋፍ ማስተባበር፤
3.7. ከኢተፖድኅ የአመራር አካል የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች መፈጸም፤

# ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 4 አዲስ አባሎችን መቀበልና ማስወጣት

ማንኛቸውም ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት
4.1. የኅብረቱን ዓላማዎች /እምነቶች መንፈሳቸውን ጭምር ተቀብሎ ተግባራዊ ሊያደርጋቸው ዝግጁ ከሆነ እና፤
X 4.2. የኅብረቱን አባል ድርጅቶች 3/4 አብላጫ ድምፅ (qualified majority)ካገኘ የኢተፖድኅ አባል ድርጅት ሊሆን ይችላል፤
4.3. ኢተፖድኅ የፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ ስለሆነ አባል ሊሆኑ የሚችሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ይሆናሉ፤

4.4. የኢተፖድኅ ዓላማዎች/እምነቶች የጣሰና ኅብረቱን የሚጻረር ተግባር የፈጸመን አባል ድርጅት ከህብረቱ ማስወጣት ይቻላል፤

4.5. የኢተፖድኅን አባል ድርጅት ከህብረቱ ለማስወጣት የሚቻለው በአባል ድርጅቶች አብላጫ ድምፅ (qualified majority) ማለትም 3/4 ድምፅ ሲገኝ ይሆናል፤

## አንቀጽ 5 የአባል ድርጅቶች መብቶች

5.1. በኅብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ውስጥ በኃላፊነት ሥፍራ ተመድቦ ሙሉ ትሳትፎ ማድረግ፤

5.2. በአስተባባሪ ኮሚቴ ለውሳኔ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ የድጋፍ ድምፅ መስጠት፤መንፈግ፤መንቀፍ፤ሃሳብ ማቅረብ፤መወያየት፤

5.3. "አንድ ድርጅት አንድ ድምፅ" በሚል መርህ መሰረት የአባልነት ድርጅታዊ እኩልነትን መጠበቅ፤ማክበር፤

5.4. ከኅብረቱ ዓላማዎች/እምነቶች ጋር ተቃራኒ እስካልሆነ ድረስ ማንኛቸውንም ነገር የማድረግ ድርጅታዊ ነጻነት መከበር፤

5.6. የኅብረቱ ውሳኔዎችና አድራጎት የአባል ድርጅትን ሕልውና የሚጎዱ ሆኖ ከተገኘ ፥ ከኅብረቱ ጭራሹኑ መውጣት፤

## አንቀጽ 6 የአባል ድርጅት ግዴታዎች

6.1. በዚህ መሠረታዊ ሰነድ መሠረት የሚተላለፉትን ዲሞክራሲያዊ ውሳኔዎች በታማኝነት መፈጸም፥ማስፈጸም፤

6.2. ኅብረቱ የተቋቋመለትን ዓላማዎች/ግቦች ከግብ ያደርስ ዘንድ ሙሉ ትብብር መስጠት፥አቅም እንደፈቀደ የገንዘብ አስተዋጽኦ ማድረግ፤

6.3. ኅብረቱን ከውስጥና ከውጪ አፍራሽ ጥቃትና አስጊ አዝማሚያ መጠበቅ፥ መከላከል፤

6.4. በአስተባባሪ ኮሚቴ ስብሰባዎች በአካል ወይም የተግባር ተሳትፎ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ መገኘት፤መሳተፍ፤

## አንቀጽ 7 የኅብረቱ የድጋፍ አካላት

7.1. ኢተፖድኅ ዓላማዎቹን/እምነቶቹን የሚቀበሉትን ወይም የሚደግፉትን የሠራተኛ፥የአርሶአደር፥ የሃይማኖት፥የሴቶች፥የወጣቶች፥የሙያ፥የማኅበረሰብና ሕዝባዊ ወይም ሌሎች ድርጅቶች በደጀንነት ያሰልፋል፤

7.2. ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችን በደጀንነት መቀበል በአባል ድርጅቶች ቀላል የድምጽ ብልጫ (simple majority)ይወሰናል፤

7.3. ኢተፖድኅ ዓላማዎቹን/እምነቶቹን የሚቀበሉትን ወይም የሚደግፉትን ድጋፍ ሰጪ አካላትን በየአገሮችና ከተሞች ያደራጃል፤

7.4. ድጋፍ ሰጪ አካላት በተለምዶ እንደሚደረገው በኢተፖድኅ ክፍት ጉባዔዎች በተመልካችነት /በአዳማጭነት ብቻ ሊገኙ ይችላሉ፡፡ የሚያቀርቧቸው ሰነዶች ካሉ ለሰብሳቢው ሊሰጡ ይችላሉ፤

## አንቀጽ 8 የኢተፖድኅ አስተባባሪ ኮሚቴ

8.1. የኅብረቱን ዓላማዎችና/እምነቶች የሚያስፈጽምና የአባል ድርጅቶችን ጥረት የሚያስተባብር አካል የኅብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ሲሆን፤ በእያንዳንዱ ድርጅት በኦፊሲዬል የሚሰየም አንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ይወከላል፤ ተወካዩ በማይገኝበት ጊዜ አባል ድርጅቱ በሚተካው ሌላ ባለሥልጣን ይወከላል፤

8.2. በኮሚቴው ውስጥ አንድ ድርጅት አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፤ ይህም ድርጅታዊ እኩልነት ኅብረቱ በሚጠራቸው ጉባዔዎች ውክልናና ድምፅ አሰጣጥ ይንጸባረቃል፤

8.3. አስተባባሰሪ ኮሚቴው የኅብረቱ ስልት አውጪ፥ፖሊሲ አመንጪ፥አስተባባሪና ከፍተኛ የአመራር አካል ሆኖ ያገለግላል፤

8.4. አስተባባሪ ኮሚቴው አዲስ አባሎችን ይቀበላል፥ያሰናብታል፥የኅብረቱን ቅርንጫፎች ያቋቁማል፤

8.5.የንዑስ ኮሚቴዎችን ሥራ ይቆጣጠራል፥ያስተባብራል፤

8.6. ኮሚቴው በአንድ አማካይ ስፍራ በሚቋቋም ጽ/ቤት ተግባሮቹን ያከናውናል፤

8.7.አ/ኮሚቴው የኅብረቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ለማከናወን ከአስተባባሪው ኮሚቴ የተውጣጣጣ አራት አባላት የሚገኙበት ቋሚ ሰክሬታሪያት ይኖረዋል፤

8.8. አ/ኮሚቴው ከሚመለከታቸው የድጋፍ አካላት ጋር በመመካከር ኅብረቱ ከድጋፍ አካላት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ፥ተሳትፎና ተዛምዶ መመሪያ ያወጣል፥በሥራ ላይ ያውላል፤

8.9. የኅብረቱ የገንዘብ አቅም እንዲዳብር ያደርጋል፥ ሂሳቡን ይቆጣጠራል፥ኦዲት ያስደርጋል፤

8.10. አሰተባባሪ ኮሚቴው ሰብሳቢ፥ ም/ሰብሳቢ፥ ዋና ጸሐፊና ገንዘብ ያዥና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የሥራ ዘርፎች ይኖሩታል፤

8.11. አ/ኮሚቴው ከብዙኃን መገናኛ አውታሮች ግንኙነት ይፈጥራል፥ድጋፍና ትብብር ይሻል፤ስብሰባና ሴሚናሮች ያዘጋጃል፥መግለጫዎች ያወጣል፤

8.12. አ/ኮሚቴው ከመንግሥታት፥ዓለማዓቀፋዊ፥አህጉራዊና መንግሥታዊ ካልሆኑና ከአገር ውስጥና ውጪ ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፥ የፖለቲካ፥ የዲፕሎማሲ፥ የገንዘብና ሁለንተናዊ ድጋፍና ትብብር ይሻል፤

8.13. አ/ኮሚቴው ኅብረቱን ወክሎ ከመንግሥታትና ዓለምዓቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ይደራደራል፤

## አንቀጽ 9 የአስተባባሪው ኮሚቴ አሠራር

9.1. የአ/ኮሚቴው ድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት አባል ድርጅቶች ቢቻል በግንባር በመገኘት፥በቴሌኮንፈረንስ ወይም በፋክስና በተጠሪ አባላት ፊርማ ይሆናል፤

9.2. ኮሚቴው የሥነ ሥርዓት(procedural)ጉዳዮችን በተራ ድምፅ ብልጫ (simple majority)ይወስናል፤

9.3.ቁምነገር ያዘሉ (substantive) ጉዳዮች በአባል ድርጅቶች የተባበረ ድምፅ(consensus) ካልተቻለ በአብላጫ ድምጽ(qualified majority) 3/4 ድምፅ ይሆናል፤

9.4.ጉዳዮች ቁምነገራዊ ወይም ሥነሥርዓታዊ መሆናቸው የሚወሰነው በአባል ድርጅቶች የአብላጫ ድምፅ (qualified majority) ነው፤

## አንቀጽ 10 የአስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ

10.1. የአስተባባሪው ኮሚቴ ሰብሳቢ ከአባል ድርጅቶች ቋሚ ተጠሪዎች መካከል በድምጽ ብልጫ ይመረጣል፤

10.2. ሰብሳቢው የኮሚቴውን ስብሰባ ይጠራል፤ የስብሰባውን አጀንዳ ከአባል ድርጅቶች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፤

10.3. መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን እንዲሁም የሴክሬታሪያቱን የሥራ እንቅስቃሴ ያስተባብራል፤

10.4. የኅብረቱ ቀዳሚ አፈ ጉባዔ ሆኖ ያገለግላል፤

10.5. በኅብረቱ ወጪ ገንዘብ ላይ ከገንዘብ ያዥ ጋር በጥንድ ይፈርማል፤

10.6. የኅብረቱን መግለጫዎች ከሴክሬታሪያቱ ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ያወጣል፤
10.7. ተጠሪነቱ ለኅብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፤
10.8. የሥራ ሪፖርት ለአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፤
10.9. የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፤
10.10. ሰብሳቢው የአስተባባሪ ኮሚቴውና የአ/ኮሚቴው ሰክሬታሪያት የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤
10.11. የኅብረቱ ምክትል ሰብሳቢ ዋናው ሰብሳቢ በሌለበት ጊዜ ለዋናው ሰብሳቢ የተሰጡትን የሥራ ድርሻዎች በኃላፊነት በመቀበል ተክቶ ይሠራል፤

## አንቀጽ 11 የአስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ

11.1. የኮሚቴው ዋና ጸሐፊ ከአባል ድርጅቶች ቋሚ ተጠሪዎች መካከል በድምጽ ብልጫ ይመረጣል፤
11.2. የኅብረቱን ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ ይይዛል፤ ውሳኔዎችን ለአባል ድርጅቶች ያሳውቃል፥ያሰራጫል፤
11.3. የኅብረቱን ሰነዶችና መዛግብት ይይዛል፤
11.4. የኅብረቱ ጽ/ቤት በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
11.5. የአገልግሎት ዘመን ለሁለት ዓመታት ይሆናል፤
11.6. የሥራ ሪፖርት በየወቅቱ ለአስተባባሪ ኮሚቴና ለሴክሬታሪያቱ ያቀርባል፤
11.7. ተጠሪነቱ ለአስተባባሪ ኮሚቴው ሆኖ፤በኮሚቴውና በሰክሬታሪያቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

## አንቀጽ 12 የአስተባባሪው ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ

12.1. ከአስተባሰባሪው ኮሚቴው አባል ድርጅቶች ቋሚ ተጠሪዎች መካከል በድምፅ ብልጫ ይመረጣል፤
12.2. ተጠሪነቱ ለአስተባባሪው ኮሚቴ ይሆናል፤
12.3. ህብረቱ ከየአቅጣጫው የሚያገኛቸውንና የሚሰበስባቸውን ገንዘብ በኅብረቱ ሂሳብ አካውንት ይቀበላል፥ ይይዛል፤
12.4. በአስተባባሪ ኮሚቴ ውሳኔና እንደ አስፈላጊነቱ በሰክሬታሪያቱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ለሚያስፈልገው ጉዳይ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ ያካፍላል፤ የእርሱና የሰብሳቢው ፊርማዎች በወጪ የገንዘብ ሰነድ ላይ መኖራቸውን ያረጋግጣል፤
12.5. የኅብረቱን ገንዘብ አያያዝ በሚመለከት መመሪያ ያዘጋጃል፥የሂሳብ ሰነዶችንና መዝገቦችን በጥንቃቄ ይይዛል፤
12.6. ስለ ኅብረቱ የገንዘብ ሁኔታ በስድስት ወር አንድ ጊዜ አጠቃላይ ሪፖርት ያቀርባል፤
12.7. ተጠሪነቱ ለአስተባባሪ ኮሚቴው ሆኖ፤ በኮሚቴውና በሰክሬታሪያቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

## አንቀጽ 13 የተለያዩ ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም

13.1. የኅብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የኅብረቱን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ኮሚቴዎችንና የሥራ ዘርፎችን ያቋቁማል፥ ያስተባብራል፤

## አንቀጽ 14 የኅብረቱን ቅርንጫፍ አካላት ማቋቋም

14.1. የኅብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የኅብረቱን ቅርንጫፍ አካላት በአህጉራትና በአገሮች በተዋረድ በከተሞች ያቋቁማል፤

14.2. የህብረቱ ቅርንጫፎች የህብረቱ አባል ድርጅቶች በሚገኙባቸው አገሮች የህብረቱ ቅርንጫፍ ይቋቋማል፤

14.3. የቅርንጫፍ አካላት አመራር በአባል ድርጅቶች ተራ በተራ (rotation) ዘይቤ ይሆናል፤

## አንቀጽ 15 <u>የኅብረቱ ምልዓተ ጉባዔ</u>

15.1. በማንኛቸውም ጉዳዮች ላይ ለመወያየትና ለመወሰን የሁሉንም የኅብረቱን አባል ድርጅቶች ተሳትፎ ከሚከተሉት በአንዱ ማለትም በአካል በመገኘት፥ በቴሌኮንፈረንስ፥ በፋክስና በስልክ ይሆናል፤

## አነቀጽ 16 <u>የኅብረቱን መሠረታዊ ሰነድ ሥራ ላይ ማዋል፤ ማሻሻል፤</u>

16.1. ይህ መሠረታዊ ሰነድ በአባል ድርጅቶች ከጸደቀና በፊርማቸው ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፤

16.2. የዚህ መሠረታዊ ሰነድ አንቀጽና ክፍሎች ሊሻሻሉ ወይም ሊለወጡ የሚችሉት በአባል ድርጅቶች አብላጫ ድምጽ(qualified majority) ወይም 3/4 ድምጽ ብቻ ነው፤

## <u>የኅብረቱ መሥራች ድርጅቶች</u>

1. የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ)

______________________________

2. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ)

______________________________

3. የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን)

______________________________

4. የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ም/ቤት(ኢሰዴኃም)

______________________________

5. የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ)

______________________________

6. የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር( ታንድ)

______________________________

7. የደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት( የደቡብ ኅብረት)

______________________________

8. የትግራይ ትግርኝ ኢትዮጵያ-ኢትዮጵያዊ ቡድን ለሶሻል ዴሞክራሲ(ትትኢ-ኢቡዴ)

______________________________

**መስከረም ፫ ፲፱፺፩ ዓ.ም. - ፓሪስ September13,1998 -PARIS**

በመጀመሪያው· የሲቪ· ተቋማት· የጋራ ስብሰባ· ዶሮሪያ

ቦ፡ ኣስመራ ፡ ከዘተከባበሩ፡ ምስ/ተሰንዳደ፡ 14/09/1998

| ተራ· ቁ· | የተወካዩ ስም· | የወከለው· ድርጅት ስም· | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | በየነ፡ ዳንኤል (ሪክሂ) | ኢ.ሠ.ዴ.ኢ.ሕ ወ/ቤተ | [signature] |
| 2 | ኢዩብ፡ ዓስማሮም( ሀ ) | ቅንጅት | [signature] |
| 3 | ኦረጋዊ በርሀ | TAND | [signature] |
| 4 | ኢዩስ፡ ወ/ሃይማኖት· | ሰ ኢ ብ ዴ ግ | Lyasu Woldehaimanot |
| 5 | ገዛኸኝ፡ ኃይሌ | ONC | [signature] |
| 6 | ነገደ ጉበዜ | ቅንጅት | [signature] |
| 7 | መዓዛ· ቀሀዬ | መኢሶን | [signature] |
| 8 | ኢሰፋ፡ ርእሶ፡ ግብረሥላሴ፡ | [illegible] | [signature] |
| 9 | [illegible] | ኢርዴፍ | |